መልእክት አንድ

## በምሳሌ በኩል የተገለጠውን እና የተላለፈውን
## የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ በተመለከተ
## በ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት ያለው ውስጠ-መሠረታዊ መገለጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ኤፌ. 1፡10፣ 22-23፤ 3፡9፤
ቆላ. 2፡9፤ 3፡11፤ 1 ጢሞ. 1፡4፤ 1 ነገ. 2፡11-12፤ 6፡1-2

**I. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መጽሐፍ ነው—ዘፍ. 1፡1፣ 26-28፤ ራእ. 21፡1-2፣ 9-11፦**

ሀ. መላው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ብሉይ ኪዳንም አዲስ ኪዳንም፣ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር አኮኖሚ ከዚያም የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ሙሉ ትርጉም እና ፍጻሜ ስዕል ነው—ኤፌ. 1፡10፤ 1 ጢሞ. 1፡4።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ማዕከሉ እና እውነታው የሆነውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ በተመለከተ የመለኮታዊው መገለጥ ዘገባ ነው—ዮሐ. 14፡6፤ ቆላ. 1፡15፤ 3፡11፦

1. ክርስቶስ የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ ነው፣ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት—2፡9፤ ኤፌ. 1፡22-23።
2. ክርስቶስ እና ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መዋቅር ናቸው—ኤፌ. 5፡32።

ሐ. እግዚአብሔር የመረጣቸውን፣ የዋጃቸውን እና ዳግም የወለዳቸውን ሕዝቡን መጀመሪያ ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡ፣ ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ በሆነ መልኩ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ያደርጋቸው ዘንድ፣ ሦስታንዱ አምላክ፣ በመለኮታዊው ሥላሴው ወደ እነርሱ ውስጥ እንደ ሕይወታቸው፣ የሕይወት አቅርቦታቸው እና እንደ ሁሉ ነገራቸው ራሱን ማደል ከሆነው እቅዱ እና አዘገጃጀቱ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ነው—ኤፌ. 3፡9፦

1. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ መሆኑን ካየን፣ እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ስናጠና ይህን ቁልፍ እንጠቀማለን።
2. ይህን ቁልፍ ካየን እና ከተጠቀምንበት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር የሆነው ነገር—የመለኮታዊው ኢኮኖሚ መገለጥ—ለእኛ ይሆንልናል—ሉቃ. 24፡44-46።

**II. አንደኛ እና 2ኛ ነገሥት ታሪካዊ ሐቆችን ሳይሆን በእነዚህ መጽሐፎች ውስጥ ያለውን ውስጠ-መሠረታዊ መገለጥ የሚመለከቱ ናቸው፦**

ሀ. ከኢያሱ እስከ አስቴር ባለው ዘገባ መሠረት የታሪኩ ውስጠ-መሠረታዊ መገለጥ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ በምድር ላይ ባሉ ምርጦቹ እንዴት እንደተከናወነ ለእኛ ለመግለጥ ነው—ኢያ. 1፡1-9፤ 1 ሳሙ. 16፡12-13፤ 1 ነገ. 2፡11-12፤ 6፡1-2።

ለ. ከውጪ ሲታዩ፣ የአንደኛ እና 2ኛ ነገሥት መጻሕፍት የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ናቸው፤ በእውነቱ፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት የተጻፉት ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ጋር በሚገናኝ መንገድ በእግዚአብሔር መንፈስ አነሣሽነት ነው—ኤፌ. 3፡9፤ 1 ጢሞ. 1፡4።

ሐ. ዳዊት እና ሰሎሞን፣ እንደ ምሳሌዎች፣ የእግዚአብሔር አካል መልበስ የሆነውን ክርስቶስን እና የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ከሚመለከተው ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ የሚገናኝ ለመሆኑ ጠንካራ ማረጋገጫዎች ናቸው—ኤፌ. 5፡32።

መ. ሰሎሞን እና በእርሱ የተገነባው መቅደስ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ጠንካራ ሚናዎችን ስለሚጫወቱ እና እንዲህ ባለው ታሪክ ውስጥ ሰፊ ክልል ስለሚይዙ፣ የእስራኤል ታሪክ በምሳሌ መንገድ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ፍጻሜ በእጅጉ የሚመለከት ስለመሆኑ ማረጋገጫዎች ናቸው—ሉቃ. 24፡44፦

1. ክርስቶስ እና ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊነት እና አጽናፍ-ዓለማዊነት መሆናቸው በአዲስ ኪዳንም በብሉይ ኪዳንም በሁለቱም አጽናፍ-ዓለማዊ ነው—ማቴ. 16፡16-18።
2. የታሪክ መጻሕፍት ክርስቶስን እና ቤተ ክርስቲያንን ከሚመለከተው ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ እይታ ነጥብ አኳያ እንደተጻፉ ማየት ያስፈልገናል—ኤፌ. 5፡32።

ሠ. አንደኛ እና 2ኛ ነገሥትን ስናነብ፣ በብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት እና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ግንኙነት ማየት ያስፈልገናል፤ ይህ ግንኙነት ለክርስቶስ እና ለክርስቶስ አካል የሆነው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ነው—ኤፌ. 1፡22-23፤ 3፡17፤ 4፡16።

**III. የብሉይ ኪዳን ታሪክ በምሳሌ መንገድ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር በጥብቅ የተገናኘ ነው—ኤፌ. 3፡9፤ 1 ቆሮ. 5፡7፤ 10፡6፡-**

ሀ. ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ስዕላዊ ማሳያ ሲሆን፣ አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ተግባራዊ ፍጻሜ ነው።

ለ. ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉት ምሳሌዎች እንደ ዘላለማዊ ኢኮኖሚው ማዕከል እና የክቡብ ዳርቻ በክርስቶስ አካል የለበሰውን ሦስታንዱን አምላክ ይገልጣሉ፣ በተጨማሪም ሦስታንዱ አምላክ ክርስቶስ ለመረጣቸው ሕዝቡ በረከት እና ሁሉ ነገር እንደሆነ ይገልጣሉ—ዘዳ. 8፡7-11።

ሐ. ከኢያሱ እስከ አስቴር ያሉት አሥራ ሁለቱ የታሪክ መጻሕፍት እንደ መልካሚቱ ምድር የተሰፋ ቃል የተገባውን ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ የራስ ለማድረግ፣ ለመውረስ እና ለመደሰት ሦስታንዱ አምላክ በመረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ ይገልጣሉ—ኢያ. 1፡1-9፣ 13፤ አስ. 4፡13-14።

መ. የግጥም መጻሕፍት—ኢዮብ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ—ክርስቶስ እግዚአብሔር የመረጣቸው ሕዝቡ ሊከታተሉት የሚገባ ልዩና ብቸኛ ፍጹምነት እና እግዚአብሔር የመረጣቸው ሕዝቡ ሊያገኙት እና ሊደሰቱት የሚገባ ልዩና ብቸኛ እርካታ እንደሆነ ይገልጣሉ—ኢዮ. 42፡1-5፤ መዝ. 2፡6-12፤ 8፡1፤ መኃ. 1፡2-4፤ 6፡1፣ 10፣ 13፤ 8፡1፣ 14።

ሠ. ከኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ ባሉት አሥራ ሰባት የትንቢት መጻሕፍት፣ ሦስታንዱ አምላክ በአዲስ ሰማይ እና በአዲስ ምድር ለሚጠናቀቀው ለዘላለማዊ ኢኮኖሚው መፈጸም ሙሉ ቤዛነቱን ለማከናወን አምላክ-ሰው እንደሆነ እናያለን—ኢሳ. 9፡6፤ ራእ. 21፡1።

ረ. ከማቴዎስ እስከ ዮሐንስ ያሉት መጻሕፍት ሦስታንዱ አምላክ ሁሉን-ያካተተ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ ለመሆን በሂደት እንዳለፈ እና እንደተጠናቀቀ ይገልጣሉ—ዮሐ. 1፡14፤ 7፡39።

ሰ. የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሁሉን-ያካተተው ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት መፍራት የእግዚአብሔር አካል መልበስ እንደሆነው እንደ የክርስቶስ እውነታ ራሱን ማሰራጨቱን ይገልጣል—1፡3፣ 8፤ 2፡22-36፤ 4፡23-31።

ሸ. ከሮሜ እስከ ራእይ ያሉት መጻሕፍት ሁሉን-ያካተተው ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ እንደ ተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ዘላለማዊ መተለቅ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እንደሚጠናቀቀው እንደ የክርስቶስ አካል፣ እንደ የተጠናቀቀው የሦስታንዱ አምላክ ሕይወታዊ አካል አድርጎ አብያተ ክርስቲያናትን በልውጠት በኩል እየገነባ እንደሆነ ይገልጣሉ—ሮሜ 1፡3-4፤ 12፡4-5፤ 16፡20፤ ራእ. 21፡2፣ 9-11።

**IV. በአንደኛ እና 2ኛ ነገሥት ያለው ውስጠ-መሠረታዊ መገለጥ በምሳሌ ተገልጦ ተላልፏል፡-**

ሀ. የእስራኤል ታሪክ የመላው ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ምሳሌም ጭምር ነው—1 ጢሞ. 1፡4።

ለ. እስራኤል ቤተ ክርስቲያንን በአዲስ ኪዳን እንዳለች የእግዚአብሔር ምርጥ በምሳሌ ያሳያል—1 ቆሮ. 5፡7፤ 10፡6፡-

1. የእግዚአብሔር ውጥን ብዙዎች የተካተቱበት አካል ማግኘት ነው—ኤፌ. 1፡22-23፡-
   ሀ. ለዚህ በእስራኤል ለተመሰለው ብዙዎች ለተካተቱበት አካል በምድር ላይ የእግዚአብሔር ቤት፣ የእግዚአብሔር መኖሪያ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር ብዙዎች ወደ ተካተቱበት እስራኤል ውስጥ ራሱን ሠራ—ዘጸ. 25፡8-9፤ 40፡34።
   ለ. ይህ ብዙዎች የተካተቱበት እስራኤል እንደ የክርስቶስ አካል የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነው።
2. የእስራኤል ታሪክ በሙሉ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነው፤ ጳውሎስ የእስራኤልን ልጆች ታሪክ ለአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ይተገብረዋል—1 ቆሮ. 5፡7፤ 10፡6።
3. ብሉይ ኪዳን ሕዝብ አለው—እስራኤል—አዲስ ኪዳንም ሕዝብ አለው—ቤተ ክርስቲያን፤ እነዚህ ሁለት ሕዝቦች እግዚአብሔር የሠራው አንድ ነገር መግለጫ ናቸው—የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም—ኤፌ. 1፡10፤ 3፡9።

ሐ. ዳዊት መከራ የሚቀበለውን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል፣ ሰሎሞን በእግዚአብሔር መንግሥት እና በእግዚአብሔር መንግሥት ግርማ የከበረውን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል—1 ነገ. 2፡11-12።

መ. መቅደሱ በአጽናፍ-ዓለም እንዳለ ልዩና ብቸኛ የእግዚአብሔር ግንባታ ክርስቶስን እና ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ ያሳያል—ማቴ. 12፡6፤ 16፡18።

ሠ. ነቢዩ ኤልሳዕ በምሳሌ የእግዚአብሔርን አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ይወክላል፤ እርሱ በአዲስ ኪዳን ያሉትን እውነተኛ ነገሮች በምሳሌ የሚያሳይ በብሉይ ኪዳን ያለ ምሳሌ ነው—2 ነገ. 4፡9።

ረ. በእጅጉ የተጠላች ማንነት የሆነችው አረማዊቷ የአክዓብ ሚስት ኤልዛቤል በአዲስ ኪዳን እውነታ ኤልዛቤል የሆነችው—የከሃዲዋ ቤተ ክርስቲያን—ምሳሌ ናት—1 ነገ. 16፡31፤ 19፡1-2 21፡23፤ ራእ. 2፡20-23።

ሰ. በምሳሌ የንጉሡ ቤተ መንግሥቶች እና የእግዚአብሔር መቅደስ የተለያዩ የነበሩ ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን እውነታ ግን እነዚህ ሁለቱ አንድ ሕንጻ ናቸው—1 ነገ. 9፡15፤ ኤፌ. 2፡21-22፦

1. በአንድ በኩል፣ እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች እግዚአብሔርን ለማገልገል እና ለማምለክ ካህናት ነን—1 ጴጥ. 2፡9።
2. በሌላ በኩል፣ ለእግዚአብሔር ለመግዛት የእግዚአብሔር ነገሥታት ነን—ራእ. 1፡6፣ 9፤ 5፡10።

ሸ. ነገሥታት የአዲስ ኪዳን አማኞች ምሳሌዎች ናቸው፣ ምክንያቱም ሁሉም የአዲስ ኪዳን አማኞች ነገሥታት ለመሆን በእግዚአብሔር ድነዋል—ራእ. 1፡6፣ 9፤ 5፡10፦

1. በአዲስ ኪዳን ያሉ አማኞች በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ያሉት የነገሥታት ምሳሌ ፍጻሜ መሆን አለባቸው—ሮሜ 5፡17፣ 21።
2. በአዲስ ኪዳን አማኞች ሁሉ የዳኑት ነገሥታት እና ካህናት ለመሆን ነው—1 ጴጥ. 2፡9፤ ራእ. 1፡6፤ 5፡10፤ 2 ጢሞ. 2፡12፦

   ሀ. እግዚአብሔር ይገዛል፣ በቀጥታ ግን አይገዛም፤ የሚገዛው ነገሥታት በሆንን በእኛ፣ በአማኞች በኩል ነው—ራእ. 20፡4፣ 6፤ 3፡21።

   ለ. በመለኮታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሰማያዊ እና ንጉሣዊ ሕይወት ዳግም ተወለድን፤ ይህም በሁሉም ነገሮች ላይ እንደ ነገሥታት ለመግዛት ያነግሠናል—ዮሐ. 1፡12-13፤ 3፡3፣ 5፤ ራእ. 5፡10፤ ሮሜ 5፡17፣ 21።

**V. የታሪክ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተቀመጡት በምሳሌ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ግልጽ እይታ ስለሚሰጡን ነው፤ የብሉይ ኪዳን ምሳሌ ውስጠ-ነገር እንደ ማዕከል እና እውነታ ከክርስቶስ እና ከአካሉ ጋር የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ነው—ኤፌ. 1፡9፤ 3፡9፤ 5፡32።**

© 2022 Living Stream Ministry